# የበቆሎ ገንፎ

(ከማህሉ በቀለ)

ምርጫው ተጭበርብሯል
የሕዝብ ድምፅ ተሰርቋል
በዚህ አይነት ውጤት፣ ፓርላማ እንግባ?
ወይንስ እንታገል፣ የወያኔን ደባ
ሆነና መንገዱ፣ የትግሉ አቅጣጫ
መከፋፈል ሆነ፣ የታጋዩ ምርጫ፡፡

ለእውነት የቆሙት፣ የሕዝብ ተመራጮች
የሙያ ማኅበራት፣ የዜና አውታሮች
የሠላም፣ የዕድገት፣ የመብት ተሟጋቾች
ይከፈሉ ጀመር፣ በመንታ መንገዶች፡፡

በውስጥም በውጭ፣ ያለው ያበሻ ሀይል
እንዲሁ ሲታመስ፣ ከጥግም ከመሀል
እንደ ገና’ ቆሎ፣ ብትንትን እያለ
በጥፋት ቁልቁለት፣ እያሽቆለቆለ
ብዙ ራስ ታመመ፣ ብዙ ሆድ ቆሰለ፡፡

የአሜሪካ ቻፕተር፣ የአውሮፓ ተጠሪ
አለም አቀፍ ቡድን፣ ትግል አስከባሪ
ይኸም ተወካይ ነው፣ ያኛውም ተወካይ
ይኸ ልታገል ባይ፣ ያኛው ልታወቅ ባይ
ሆነና ሥራችን፣ ነገር ተንከርፍፎ
የትግሉ አቅጣጫ፣ ተጣሞ ተንሻፎ
ፖለቲካው ሆኗል፣ የበቆሎ ገንፎ፡፡

እህሉ ተፈጭቶ
በወንፊት ተጣርቶ
በፈላ ውሃ ውስጥ፣ እየተበተነ
እየተላቆጠ፣ እየተማሰለ
ጥሬነቱ ቀርቶ፣ መብሰሉ ሲታወቅ
ይነሳል ከእሳት ላይ፣ እንደቂጣ ሳይደርቅ፡፡

የገንፎ አሰራር፣ ይህንን ይመስላል
ጨምለቅለቅ ማድረግ ነው፣ ምኑ ያስቸግራል
ቢሆንም ማባያ፣ ማጣፈጫ ቅመም
በርበሬም ይሁን ጨው፣ ዘይትም ሆነ ቅቤ
ካልተጨመረበት
ገንፎ ጨምላቄ ነው፣ ጣዕም የሌለበት፡፡

ዱቄቱን ውሃውን፣ የሚይዘው ድስት’
ሙቀቱን አመንጭው፣ ታላቁ እሳት’
ለወስወስ አድራጊው፣ ማማሰያ እንጨት’
ጠንካራ ጉልቻ፣ የሚችል ክብደት’
አብስሎ ሲያበቃ፣ በገንፎ አናት’
የሚያሰማ ቅቤ፣ ጠብ ካላለበት’
ገንፎ ጨምላቄ ነው፣ የታወቅንበት’፡፡

የኛ ፖለቲካ፣ ትርምስምስ እያለ
ከተጨማለቀ፣ ገንፎ ከመሰለ
ለኢትዮጵያ የሚሆን፣ አንድ መላ አለ፡፡
        አረ መላ መላ፣ አረ መላ
        አንፈልግም ሁለት፣ ከአንድ ሌላ!
አንድ ድምፅ ከሌለን፣ የሚሰማን የለም
ጠላት ክፍፍል ነው፣ አንድነት አይደለም፡፡

የኛም ፖለቲካ፣ ገንፎ እንዳይሆን’
በመቻቻል መንፈስ፣ ባንድ ላይ ሆነን’
ኢትዮጵያን እናውጣ፣ ከመለስ መንጋጋ
ነፃነት እንዲያብብ፣ አገር እንዲረጋ፡፡

አብዛኛው አበሻ፣ አገሩን ይወዳል
ዛሬም እንደድሮው፣ ይጎዳል ይሰዋል
ኢትዮጵያን የምወዳት፣ ካንተ በላይ እኔ
መሆኑን እወቀው፣ እያለ ወገኔ
ፍትጊያው ሽኩቻው፣ ትርምሱ በዝቶ
ወያኔን አገዝነው፣ እንዲገዛን ኮርቶ
በሥልጣን ዙፋን ላይ፣ እንዲያ ተንሰራፍቶ፡፡

ወያኔን የበጀው፣ የኛ ክፍፍል ነው
ሌላ ተአምር የለም፣ ሚስጥሩ ይኸው ነው!